ብሄራዊ መግባባት በኢትዮጵያ፡
ዘላቂ ሰላም ፣ ሀገራዊ አንድነት እና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር

(National Dialogue in Ethiopia:
Sustainable peace, National Unity and Democratic Transition)

አብዱልቃድር አደም (ዶ/ር)
ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሊቀመንብር

ነሀሴ 30፣ 2012
አዲስ አበባ

ይዘት

- ክፍል 1፡ ብሄራዊ መግባባት ጽንሰ ሀሳብ (Conceptual framework)
  - 1.1 ትርጉም እና ዋና ዋና ዓላማዎች
  - 1.2 የብሄራዊ መግባባት ይዘት/ማዕቀፍ
  - 1.3 ብሄራዊ መግባባት፡ የስኬት እና ውድቀት ሰበቦች
  - 1.4 ብሄራዊ መግባባት እና ሌሎች ፖለቲካዊ የችግር መፍቻ መሳሪያዎች፡ ንጽጽር

ይዘት...የቀጠለ

- ክፍል 2፡ ብሄራዊ መግባባት በኢትዮጵያ፡
  - 2.1 አሰገዳጅ ምክንያቶች
  - 2.2 ዓላማ
  - 2.3 የጊዜ ሰሌዳ/ገደብ
  - 2.4 የብሄራዊ መግባባት ተሳታፊዎች
  - 2.4 አጀንዳዎች
- ክፍል 3፡ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ
- ክፍል 4፡ ማጠቃለያ

1.1 ብሄራዊ መግባባት፡ ትርጉም

- ብሄራዊ መግባባት በአንድ ሀገር ውስጥ ባሉ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ተዋናዮች እና ባለድርሻ አካላት መካከል ጥልቅ የፖለቲካ ቀውስን ለማስወገድ፣ ጦርነትን ለማስቆም ወይም የተሳካ የፖለቲካ ሽግግር ለማካሄድ በአንድ ሀገር ባለቤትነት የሚካሄድ የፖለቲካ ሂደት ነው።

- “nationally owned political processes aimed at generating consensus among a broad range of national stakeholders in times of deep political crisis, in post-war situations or during far-reaching political transitions” (Blunck et al., 2017, p. 21).

ብሄራዊ መግባባት ባህሪያት... የቀጠለ

- ልዩ ልዩ የፖለቲካ ተዋናዮች/ባለድርሻ አካላት መካከል የሚካሄድ፣
- **ጥልቅ የፖለቲካ ቀውስን ማስወገድ፣**
- ጦርነትን ለማስቆም ወይም፣
- **የተሳካ የፖለቲካ ሽግግር ማካሄድ፣**
- **በአንድ ሀገር ባለቤትነት** የሚካሄድ፣

ትርጉም የቀጠለ....

- ብሄራዊ መግባባት ነጠላ ሁነት (Singular event) ሳይሆን ረዥም ጊዜ የሚፈልግ የለውጥ ሂደት ነው።

ብሄራዊ መግባባት፡ ዋና ዋና ዓላማዎች

1. ቀውስ መከላከል እና ማስተዳደር (የአጭር ጊዜ)
2. ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት (ረዥም ጊዜ)

ብሄራዊ መግባባት፡ ዋና ዋና ዓላማዎች፡ የቀጠለ

- ከፍተኛ የፖለቲካ፣ የባህል ግጭቶችን ማስወገድ
- የጦርነት ስጋትን ማምከን፣
- የፖለቲካ ስርዓቱን ማሻሻል (ሀገ መንግስት ማሻሻል)
- የመንግስት እና የዜጎችን ግንኙነት ማደስ/መልሶ መገንባታ (New social contract)
- ታሪካዊ ቁርሾዎችን ማከም፣
- ወዘተ

1.2 የብሄራዊ መግባባት ይዘት (Framework)

1. የብሄራዊ መግባባት እንዴት እና በማን ይጀመራል?
2. የብሄራዊ መግባባት ምእራፎች
3. ብሄራዊ መግባባት፡ የስልጣን ገደብ እና አጀንዳ
4. በብሄራዊ መግባባት ተሳታፊዎች፡ አይነት እና ብዛት
5. የጊዜ ገደብ
6. ውሳኔ አሰጣጥ
7. አወያዮች/አመቻቾች
8. ሎጂስቲክ እና ፋይናንስ

የብሄራዊ መግባባት እንዴት እና በማን ይጀመራል?

- ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃውሞ፣
- በየጊዜው የሚሰፋ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣
- የፖለቲካ ማሻሻያ ወይም የስርአት ለውጥ ጥያቄ፣
- የፍትህ መጓደል፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊነት፣
- ህዝብ በመንግስት ላይ እምነት ማጣት እና ተስፋ መቁረጥ፣
- ግቡን የሳተ የለውጥ ሂደት፣
- በፖለቲካ ልሂቃን መካከል እምነት መጥፋት፣
- በቡድኖች መካከል ግጭት፣ የዜጎች ህይወትና ንብረት መጥፋት መፈናቀል፣
- በጎረቤት/በሌሎች ሀገሮች የሚደረግ ፖለቲካዊ የለውጥ እንቅስቃሴ
- ወዘተ……

የብሄራዊ መግባባት እንዴት እና በማን ይጀመራል?...የቀጠለ

- በመንግስት
- በተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች
- በሲቪክ ማህበራት
- በልሂቃን ድርድር (elite negotiation)
- በውጭ ኃይሎች ጥያቄ እና ግፊት፣

- የብሄራዊ መግባባት ሂደት መደበኛ (Formal) ወይም ኢ-መደበኛ (Informal) በሆነ መንገድ ሊጀመር ይችላል::

የብሄራዊ መግባባት እንዴት እና በማን ይጀመራል?... የቀጠለ

- መንግሰት፡
  - የተመናመነ የቅቡልነት ጥያቄን መልሶ ለማግኘት
- ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች፡
  - የመንግስትን አወቃቀር ለመቀየር፣ አዲስ የኃይል ሚዛን ለመፍጠር፣
- ሲቪክ ማህበራት፣ ልሂቃን...
  - ልዩ ልዩ ፍላጎት፡ ያለውን ስርአት ለመቀየር የሚደረገውን ሂደት ለማፋጠን ወይም ለማዘግየት
- የውጭ ኃይላት
  - የየሀገራቱን ጥቅም ማስጠበቅ
- **የጋራ ፍላጎት፡**
  - **ብጥብጥን ፣ ደም መፋሰስን፣ የዜጎችን ሰቆቃ፣ የጦርነት ስጋትን ወዘተ ማስቆም**

የብሄራዊ መግባባት ምእራፎች:
(Phases of National Dialogue)

- ሶስሰ ዋና ዋና ምእራፎች
  1. **የዝግጅት ምዕራፍ**
  2. **ብሄራዊ መግባባት ሂደት**
  3. **የትግበራ ምዕራፍ**

የብሄራዊ መግባባት ምእራፎች: የቀጠለ

- እርስ በርሳቸው በእጅጉ የተቆራኙ እና በተግባር አንዱን ከሌላው ለመለየት የማይቻል፣
- ለሁልም ቦታ/ሀገር እና ጊዜ የሚሰራ ቀመር የለም (There is no one-size-fits-all format)
- ሁሉም ምእራፎች እንደ ሀገሩ ተጨባጭ ሊዘጋጁ ይገባል፣
  - ሆኖም የሌሎች ሀገሮች የብሄራዊ መግባባት ተሞክሮ ተቃሚ ይሆናል፣

- የዝግጅት ምእራፍ
  - የዋናው ውይይት አካል (mini-negotiation) ሲሆን በራሱ የፖለቲካ ድርድር (political bargaining process) ነው፣
  - የብሄራዊ መግባባት ቅቡልነት ይወስናል፣
  - በቂ የዝገጅት ጊዜ ያስፈልጋል- የዝግጅት ምእራፉ ከዋናው ምእራፍ ሊረዝም ይችላል፣
  - ወሰኝ ተግዳሮቶች መለየት እና የመፍትሄ ሀሳብ ማስቀመጥ፣
  - ሂደቱን የሚያስተባብር ተቋም እና ሎጂስቲክስ ማግኘት፣
  - ሌሎቹን ሁለት ምእራፎች እጣ ፋንታ ይወስናል፣

የዝግጅት ምዕራፍ፡ መተማመን መፍጠር/ማጎልበት

- መተማመን እና አቅም የሚገነባበት ምእራፍ፡
- ውጥረት እና አነስተኛ መተማመን የሚታይበት፣
  - **ተቃዋሚዎች የመንግስትን፣ መንግስት የተቃዋሚዎችን ቁርጠኝነትና እውነተኛነት ይጠራጠራሉ፣**
  - **የሲቪል ማህበረሰብ አባላት ከሂደቱ የመገፋት ስጋት፣**

- በዝግጅት ምእራፍ ውስጥ የሚመለከታቸው አካላት በበቂ ሁኔታ መወከላቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣
- የዝግጅት ምእራፍ አስተባባሪዎች እና **<u>ሰብሳቢ</u>** ወሳኝ ነው፣
- የፖለቲካ እስረኞችን መፍታት፣ የትጥቅ ትግል ለሚያደርጉ መሪዎች ይቅርታ ማድረግ (በጊዚያዊነትም ቢሆን)፣
- ጊዚያዊ የተኩስ አቁም ስምምነት ማድረግ (ታጣቂ ኃይሎች)፣
- በቂ መረጃ ማቅረብ እና የሚዲያ ነጻነትን ማረጋገጥ፣

የዝግጅት ምዕራፍ፡ የቀጠለ.....

- በዝግጅት ምዕራፍ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች
  - የብሄራዊ መግባባት አድማስ እና ገደብ፣
  - የብሄራዊ መግባባት አጀንዳዎች፣
  - ተሳታፊዎች (ዓይነት እና ብዛት)፣
  - አወያይ ወይም አመቻች (Convener)
  - የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት፣
  - ሎጂስቲክ እና ፋይናንስ፣

ምእራፍ ሁለት፡ የብሄራዊ መግባባት

- የዝግጅት ምእራፍ በተሳካ/በተሟላ ሁኔታ ሲጠናቀቅ የሚጀመር፣
- ዋናው ምእራፍ፣
- ይበልጥ ይፋ የሚሆነው ምእራፍ፣
- ቀደም ሲል በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት
  - ተሳታፊዎች ይመረጣሉ፣
  - ታማኝ አመቻች ይመረጣል፣
  - አጀንዳ ይቀረጻል/ይጸድቃል፣
- ዝርዝር የአሰራር ደንቦች እና የስራ ሂደት ይወሰናል፣
- አጋዥ መዋቅሮች (Support structures) ይቋቋማሉ፣
- ህብረተሰቡ በሂደቱ በተለያየ ደረጃ በንቃት ይሳተፋል፣
- የችግር መፍቻ ስርአቶች መቀየስ፣
- በተመረጡ አጀንዳዎች ላይ በሁሉም እርከኖች ውይይት ይካሄዳል፣

ብሄራዊ መግባባት የሚካሄድባቸው እርከኖች

- **ከፍተኛ እርከን፡**
  - ከፍተኛ ተሰሚነት እና እውቅና ያላቸው አካላት የሚሳተፉበት፣
  - ከፍተኛ የመንግስትና የፖለቲካ ድርጅቶች አመራሮች፣ ከፍተኛ የሀይማኖት መሪዎች፣ ሀገር አቀፍ እውቅና ያላቸው ግለሰቦች ወዘተ...

- **መካከለኛ እርከን፡**
  - በሚወክሉት ማህበረሰብ/ቡድን እውቅና እና ተቀባይነት ያላቸው አካላት
  - የብሄር፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ ምሁራን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ወዘተ፣

- **ታችኛው እርከን (Grass root)**
  - የአካባቢ መሪዎች፣ ብዙሀን ድርጅቶች ተወካዮች፣ ማህበራት፣ ወዘተ

ውጤታማ ብሄራዊ መግባባት መለኪያዎች

- የውይይቱ ውጤት የተሳታፊዎችን እና የህዝቡን ፍላጎት እና ቁጭት መመለስ፣
- የሚመለከታቸው አካላት የሂደቱ እና የውጤቱ ባለቤት መሆን (Ownership)፣
- መተማመን (Trust)
- ግልጽ የአተገባበር ስልት እና አደረጃጀት፣ የቁጥጥር እና ክትትል ስርአት መኖር፣
- ስምምነቶች በነጻነት እና ያለግፊት መድረስ፣
- “Constructive Ambiguity”: Henry kissinger

የትግበራ ምእራፍ (Implementation Phase)

- በብሄራዊ መግባባት ስምምነት የተደረሰባቸው ውሳኔዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፣
- አተገባበር፡ ከቀላል ወደ ከባድ
- ግልጽ እና ዝርዝር የትግበራ የጊዜ ሰሌዳ ሊኖር ይገባል፣
- የብሄራዊ መግባባት ሂደቱ ግልጽነት እና አሳታፊነት ውሳኔዎች በትክክል እንዲተገበሩ ያግዛል፣
- ከዋናው ምእራፍ የበለጠ ሀብት እና ጉልበት ሊፈልግ ይችላል፣

የትግበራ ምእራፍ..... የቀጠለ

- ውሳኔዎች በትክክል ይተገበሩ ዘንድ በዝግጅት ምእራፍ የአተገባበር እና የቁጥጥር ስርአት ሊቀመጥ ይገባል፣
- ለህዝብ በቂ መረጃ መስጠት እና ግንዛቤ መፍጠር ውሳኔዎች እንዲተገበሩ ያግዛል፣
- ውሳኔዎች በመደበኛ ወይምአዲስ በሚቋቋሙ ተቋማት አማካኝነት ተግባራዊ ይደረጋሉ፣

የትግበራ ምእራፍ..... የቀጠለ

- አንዳንድ ተሳታፊዎች የማይፈል ጓቸው/ ያልተስማሙባቸው ውሳኔዎች እንዳይተገበሩ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ፣
- የተሳታፊዎች ቁርጠኝነት የሚታይበት ምእራፍ ነው፣
- የትግበራ ምዕራፍ የሂደቱ የመጨረሻ (Closing down) ሳይሆን ቀጣይነት ያለው የውይይት ባህል ለማዳበር አዲስ ምዕራፍ የሚከፈትበት (Opening up) ነው።

የትግበራ ምእራፍ..... የቀጠለ



የሚታዩ እና የማይታዩ ውጤቶች

(Tangible and intangible outcomes)

- **የሚታዩ ውጤቶች (Tangible outcomes)፡**
  - በተቀመጡት አጀንዳዎች ላይ የተደረሱ ተጨባጭ ስምምነቶች/ውጤቶች።
  - በውይይቱ ሪፖርት (Communiqué) ይገለጻሉ፣
    - የፖለቲካ ለውጥ (መዋቅራዊ ለውጥ፣ ስልጣን መጋራት...)፣
    - የሀገ መንግስት ማሻሻያ፣
    - ነጻ እና ፍትሀዊ ምርጫ ማካሄድ፣
    - የመንግስት ለውጥ (የሽግግር መንግስት)፣
    - ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ (የመሬት ስሪት...)፣
    - ታሪካዊ ቁርሾዎችን ማረቅ፣
    - የተሰካ ሽግግር ማካሄድ፣
    - ወዘተ

የማይታዩ ውጤቶች(intangible outcomes)፡

- ቀድሞ ያልታሰቡ የጎንዮሽ ውጤቶች፣
- በግልጽ የማይታዩ ና ለመለካት የሚያስቸግሩ፣
  - ምሳሌ፡ የአስተሳሰብ ለውጥ፣ የውይይት ባህል መዳበር፣ በተሳታፊዎች መካከል የተሻለ ግንኙነት መፍጠር፣ የተሰሰቱ አመለካከቶችን መስበር፣ የልምድ ልውውጥ፣
  - የማይታዩ ውጤቶች፡ ስምምነቶችን በተሻለ ለመተግበር ያግዛሉ
  - የማይታዩ ውጤቶች ከሚታዩት ሊበልጡ ይችላሉ፣

የብሄራዊ መግባባት ተሳታፊዎች

- የብሄራዊ መግባባት ተሳታፊዎች እንደየ ሀገሩ፣ የውይይቱ ዓላማ እና ሌሎች ተጨባጭ ሁኔታዎች ይወሰናል።
- በአብዛኛው፡
  - መንግስት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የኃማኖት ተቋማት፣ ምሁራን፣ የሙያ ማህበራት፣ የንግዱ ማህበረሰብ፣
- **የተሳታፊዎች ብዛት መመዘኛ፡** ውጤታማነት እና አካታችነት (efficiency & inclusiveness)

የተሳታፊዎች መምረጫ መመዘኛ

- የድርጅት አባልነት (ፖለቲካ ፓርቲ፣ የሙያ ማህበር፣ የትምህርት ተቋም….)
- ማህበራዊ እና ስነ ሕዝብ (Social and Demographic aspects)
- አቅም፣ ታዋቂነት እና ተሰሚነት
- ስልታዊ ወይም ተግባራዊ ሁኔታዎች
- የሁሉም ቅይጥ

ውጤታማ ተሳትፎ፡ ‘በሂደት’ እና ‘በውጤት’

- ‘በሂደት’ እና ‘በውጤት’
  - **በሂደት መሳተፍ**፡ በዝግጅት እና በዋናው ውይይት በንቃት መሳተፍ፣
  - **በውጤት መሳተፍ**፡ በውሳኔ ላይ በፍቃደኝነት እና ያለምንም ጫና መሳተፍ፣

የጊዜ ርዝመት (Duration)

- የጊዜውን ርዝመት የሚወስኑ ጉዳዮች
  - የውይይቱ ዓላማ፣ ተልእኮ፣ አጀንዳ፣ አድማስ…
  - የአጀንዳዎች አጣዳፊነት፣
  - የፖለቲካ ሁኔታ፣
  - ድጋፍ ሰጭ (ገንዘብ፣ ሎጂስቲክስ) አቅርቦት፣

ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት

- በአጀንዳዎች ላይ ውስኔ ለማሳለፍ ቁልፍ ሚና ዓለው፣
- ሂደቱን ሊያፋጥን ወይም ሊያ ጓትት ይችላል፣
- በአግባቡ የተሰናዳ የውሳኔ አሰጣጥ ስርአት የባለቤትነት ስሜትን ይጨምራል/ይቀንሳ፣
- ውሳኔ በስምምነት፣ በአብላጫ ድምጽ ወዘተ...ሊሰጥ ይችላል፣

አመቻቾች

- ገለልተኛ እና በተሳታፊዎች ተአማኒ፣
- በሂደቱ ቅርጽ፣ ይዘት እና ውጤት ላይ ከፍተኛ ሚና አላቸው፣

ፋይናንስ፣ ሎጂስቲክስ

- የስብሰባ ቦታ እና የጽህፈት መሳሪያ፣
- የተሳታፊዎች መቆያ፣
- ትራንስፖርት፣
- ደህንነት እና ጥበቃ (Safety/Security)
- የባለሙያ ድጋፍ ወዘተ….
  - **መንግሰት**
  - **ዓለምአቀፍ ማህበረሰብ/ተቋማት**
  - **ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች (ሀገር ውስጥ/ የውጪ)**
  - **ተ.መ.ድ ድርጅቶች (UN Agencies)**
  - **በተናጠል ወይም በጋራ**

1.3 ብሄራዊ መግባባት፡ የስኬት እና ውድቀት ሰበቦች

- ፖለቲካዊ ምክንያቶች (Political factors)
- ሂደት ተኮር ምክንያቶች (Process factors)

ብሄራዊ መግባባት፡ የስኬት እና ውድቀት ሰበቦች.... የቀጠለ

- **ፖለቲካዊ ምክንያቶች (Political factors)**
  - የፖለቲካ ፍላጎት፣
  - የሊሂቃን ድጋፍ ወይም ተቃውሞ፣
  - የፖለቲካ መሪዎች የአጀንዳ ቅርርብ፣
  - ህዝባዊ ድጋፍ፣
  - ያለፈ የውይይት ተሞክሮ እና የውይይት ባህል፣
  - የውጭ ኃይሎች ሚና እና ድጋፍ፣

ብሄራዊ መግባባት፡ የስኬት እና ውድቀት ሰበቦች.... የቀጠለ

- **ሂደት ተኮር ምክንያቶች (Process factors)**
  - የተሳታፊዎች አመራረጥ እና ቁጥር፣
  - መተማመን ለመፍጠር የሚሰሩ ስራዎች፣
  - የውስኔ አሰጣጥ ስርአት፣
  - የሰብሰቢ/የአመቻቾች አመራረጥ፣
  - ለሂደቱ የሚደረግ የቴክኒክ ድጋፍ፣
  - በተሳታፊዎች መካከል የሚኖር ግንኙነት፣

1.4 አማራጭ የፖለቲካ ቀውስ መፍቻ መሳሪያዎች: **ንጽጽር**

- ብሄራዊ መግባባት አንድ አይነት የችግር መፍቻ መሳሪያ ነው፣
- አማራጮች ፣
    1. **ድርድር (Negotiation)**
    2. **ሽምግልና (Mediation)**

- ሶስቱ አማራጮች በጋራ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፣
- **ብሄራዊ መግባባት**
  - ከውጤት ይልቅ ሂደት ላይ ያተኩራል፣
  - ሰፊ መሰረት ያለው ተሳትፎ፣
  - የተገደበ የውጪ ኃይሎች ተሳትፎ/ሚና፣

1.4 አማራጭ የፖለቲካ ቀውስ መፍቻ መሳሪያዎች



ድርድር፣ ሽምግልና እና ብሄራዊ መግባባት

ድርድር	ሽምግልና	ብሄራዊመግባባት
		

ውጤት ተኮር ሂደት

ክፍል 2፡ ብሄራዊ መግባባት በኢትዮጵያ

- 2.1 አሰገዳጅ ምክንያቶች
- 2.2 ዓላማ
- 2.3 የጊዜ ሰሌዳ/ገደብ
- 2.4 የብሄራዊ መግባባት ተሳታፊዎች
- 2.5 አጀንዳዎች
- 2.6 ለብሄራዊ መግባባት የተደረጉ ሙከራዎች

ብሄራዊ መግባባት በኢትዮጵያ... የቀጠለ

- **2.1 አሰገዳጅ ምክንያቶች፡ ታሪካዊ/ነባር እና አሁናዊ ምክንያቶች**
  - **ታሪካዊ/ነባር ምክንያቶች/ተግዳሮቶች**
    - ተገዳዳሪ የሀገረ መንግስት/ብሄር ግንባታ ትርክት፣
    - ዋልታ ረገጥ የፖለቲካ አጀንዳ፣ ባህል፣ ዓላማ፣
    - በፖለቲካ ኃይሎች መካከል አለመተማመን እና ጥላቻ፣
    - ጽረ-ዴሞክራሲያዊ ስርአቶች የፈጠሩት ቀውስ/ውርስ፣
    - የመንግስት እና የዜጎች ኢፍትሀዊ መስተጋብር፣
    - ድህነት እና ፍትሀዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍል፣
    - የማንነት/ የብሄር ጥያቄ፣
    - አግላይ የፖለቲካ ስርአት እና የተዛባ የስልጣን ክፍፍል፣
    - ታሪካዊ የተበዳይነት ስሜት (Real or Perception)

አሰገዳጅ ምክንያቶች...

- **አሁናዊ ምክንያቶች/ተግዳሮቶች**
  - የግጭቶች መበራከት፡ የዜጎች ሞት፣ መፈናቀል፣ ንብረት መጥፋት...፣
  - የብሄር እና “የኃይማኖት” ግጭቶች መበራከት፣
  - ሀገራዊው የለውጥ/ሪፎርም ሂደት ከዜጎች ፍላጎት ጋር መጋጨት፣
  - በለውጥ ማግስት የተሸሻለው የፖለቲካ ምህዳር መልሶ “የመጥበብ” አዝማሚያ፣
  - ምርጫ 2012 መራዘም፣
  - በፌደራል እና በክልል መንግስታት እንዲሁም በክልል መንግስታት መካከል ያሉ ግጭቶች፣
  - ስራ አጥነት ፣ የኑሮ ውድነት፣ የመልካም አስተዳደር ጉድለት፣

2.2 ብሄራዊ መግባባት በኢትዮጵያ... **ዓላማ**

- **አጭር ጊዜ ዓላማዎች**
  - ሰላም እና መረጋጋትን ማስፈን፣
  - በፖለቲካ ታይሎች መካከል መተማመን መፍጠር፣
  - ቀጣዩ ሀገር አቀፍ ምርጫ ሰላማዊ እንዲሆን ማድረግ፣
  - የኢትዮጵያን አዲስ የፖለቲካ ፍኖተ ካርታ መንደፍ፣
  - የተዛነፈውን የለውጥ/ ሪፎርም/ ሂደት ማረቅ፣

ብሄራዊ መግባባት በኢትዮጵያ... **ዓላማ**

- **የረዥም ጊዜ ዓላማዎች**
  - በምንግስት እና በዜጎች መካከል አዲስ መስተጋብር መፍጠር (new social contract)፣
  - የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ፣
  - አዳዲስ የፖለቲካ ተቋማትን መገንባት፣
  - ህገ መንግስት ማሻሻል፣

2.3 የብሄራዊ መግባባት የጊዜ ገደብ

- የብሄራዊ መግባባት ከቀጣዩ ምርጫ በፊት ሊጠናቀቅ ይገባል.
  - ምርጫው ሰላማዊ እና ውጤቱም ቅቡልነት እንዲያገኝ፣
  - ድህረ ምርጫ የሀገሪቱን ፖለቲካ ሰላማዊ ለማድርግ፣
- ሂደቱን ለመጀመር ፈጣን ውሳኔ ይሻል
- የመንግስት እና የተፎካካሪ ፓርቲዎች ፍላጎት እና ቁርጠኝነት ወሳኝ ነው፣
- ብሄራዊ መግባባት ሳይፈጠር ምርጫ ማካሄድ ለባሰ ግጭት እና የፖለቲካ ቀውስ ሊያጋልጥ ይችላል፣

2.4 የብሄራዊ መግባባት ተሳታፊዎች፣

- እውቅና ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች፣
- አግባብነት ያላቸው ከፍተኛ የመንግስት ተቋማት/ኃላፊዎች፣
- የሲቪክ ማህበራት፣
- የሀይማኖት ተቋማት፣
- ከፍተኛ የትምህርት እና የምርምር ተቋማት፣
- የሙያ እና ህዝባዊ ማህበራት፣
- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተወካዮች፣

2.5 አጀንዳ፣

- የሀገረ መንግስት/ ብሄረ መንግስት ግንባታ ሂደት ታሪክ፣
- ብሄራዊ ምልክቶች (ባንዲራ፣ ጀግኖች፣....)
- የህገ መንግስት፣ የተቋም እና የህግ ማሻሻያ፣
- ጠቃላላ ምርጫ (የምርጫ ህግ)፣
- ፌዴራሊዝም ፣
- የመሬት ስሪት፣
- መንግስት እና ሀይማኖት ግንኙነት፣
- ድህነት ቅነሳ እና ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል፣
- መልካም አስተዳደር፣
- የውጭ ጉዳይ እና ብሄራዊ ደህንነት፣
- የክልልነት ጥያቄ፡ የዋና ከተማ (አ.አ.) አስተዳደር፣
- የድንበር እና የማንነት ጥያቄ፣
- የአናሳ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች ሁኔታ፣
- የመሀል እና ዳርቻ አካባቢዎች ግንኙነት (Center Periphery Relations)
- ሌሎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ አጀንዳዎች፣

2.6 ለብሄራዊ መግባባት የተደረጉ ሙከራዎች

- በታሪክ ብሄራዊ መግባባት ለመፍጠር የተደረገ ወሰኝ ሙከራ የለም፣
- ተከታታይ መንግስታት በራሳቸው አጀንዳ እና ፍላጎት ሀገሪቱን አስተዳድረዋል፣
- ነባር እና አዳዲስ ችግሮችን/ቁርሾዎችን ለምፍታት ፍላጎት እና ተነሳሽነት አልነበራቸውም፣

ለብሄራዊ መግባባት የተደረጉ ሙከራዎች... የቀጠለ

- ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሀሳቡ በተለያዩ አካላት ቀርቧል
  - የፖለቲካ ፓርቲዎች፣
  - የተለያዩ ተቋማት
  - ሙሁራን እና ታዋቂ ግለሰቦች
  - የሚዲያ ተቋማት
  - የምርምር ተቋማት
  - የውጪ መንግስታት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች

ክፍል 3፡ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ

- ብሄራዊ መግባባት ረዥም ታሪክ ያለው የፖለቲካ ቀውስ መፍቻ መሳሪያ ነው፣
- ተቀባይነቱ እየጨመረ መጥቷል፣
- የአሜሪካ ሀገ መንግስት ዝግጅት (1787) የብሄራዊ መግባባት ውጤት እንደሆነ ይታመናል፣
- ከ1950ዎቹ በኃላ ከቅኝ ግዛት ነጻ የወጡ ሀገሮች ተጠቅመውታል፣
- በ1970ዎቹ እና 1980ዎቹ በደቡብ አውሮፓ (ፖርቹጋል እና ስፔን) ደቡብ ምስራቅ አስያ ሀገሮች (ደቡብ ኮሪያ፣ ፊሊፒንስ) ጥቅም ላይ ውሏል፣
- በ1990ዎቹ በብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ብሄራዊ መግባባት ተካሂዷል፣

ዓለም አቀፍ ተሞክሮ፡ የቀጠለ

- ባለፉት 20 አመታት በተለያዩ ሀገራት በስፋት ተተግብሯል፡
  - ደቡብ አፍሪካ (1993)
  - አፍጋኒስታን (2002, 2003–2004)
  - ሶማሊያ (2000, 2002–2004),
  - ኢራቅ (2004)
  - ኬኒያ (2008)
  - ኔፓል (2008–2012)
  - ባህሬን (2011)
  - ግብጽ (2011)
  - የመን (2014)
  - ቱኒሲያ (2013–2014)
  - ሱዳን (2014–2016)
  - ቡሩንዲ (2015–2016)

ብሄራዊ መግባባት ለመጀመር ምክንያቶች

የልሂቃን ድርድር	ህዝባዊ አመጽ/ተቃውሞ	ጦርነት/ የትጥቅ ትግል
አፍጋኒስታን	ቤኒን	**አፍጋኒስታን**
ሜክሲኮ	ግብጽ	ዲ.ሪ. ኮንጎ
ኔፓል	ማሊ	ሜክሲኮ
ሶማሊያ	ሜክሲኮ	ኔፓል
የመን	ደቡብ አፍሪካ	ጊኒ
	ቶጎ	ሶማሊያ
	የመን	ሶማሊላንድ
		የመን

ብሄራዊ መግባባት አጀማመር

ተ.ቁ	ሀገር	ጀማሪ
1	ኬንያ	ኬንያ ጥምር መንግስት እና የአፍሪካ ታዋቂ ግለሰቦች ፓነል
2	ሱዳን	ፕ/ር ኡመር አልበሽር
3	አፍጋኒስታን	ቦን ስምምነት (ጀርመን)
4	ቱኒሲያ	The quartet: አራት ሲቪክ ማህበራት
5	የመን	GCC; Gulf Cooperation Council

ብሄራዊ መግባባት፡ ስያሜ

ተ.ቁ	ሀገር	ዓመት	ስያሜ
1	አፍጋኒስታን	2002	Emergency Loya Jirga (ELJ)
		2003-2004	Constitutional Loya Jirga (CLJ)
2	ቢኒን	1990	Conference of the Vital Forces of the Nation
3	ዲ.ሪ. ኮንጎ	2001–2003	Inter-Congolese Dialogue
4	ግብጽ	2011	National Dialogue
5	ማሊ	1991	National Conference
6	ሜክሲኮ	1995–1996	San Andres Dialogues
7	ኔፓል	2008–2012	The Constituent Assembly
8	ሶማሊያ	2000	The Somali National Reconciliation Conference (Djibouti process)
9		2002–2004	The Somalia National Peace Conference (Eldoret/Mbagathi process)
10			

የተሳታፊዎች ብዛት

ተ.ቁ	ሀገር	የተሳታፊዎች ብዛት
1	አፍጋኒስታን	502
2	ባህሬን	300
3	ቤኒን	520
4	ቦሊቪያ	255
5	ማእከላዊ አፍሪካ ሪፖብሊክ	20,000
6	ኮሎምቢያ	74
7	ጓቲማላ	84
8	ኢራቅ	1200-1500
9	ዮርዳኖስ	52
10	ኬኒያ	8

የጊዜ ሰሌዳ

- **ሰምንት፡** ግብጽ
- **ሰምንት-ወር፡** አፍጋኒስታን፣ ቤኒን፣ ማሊ፡
- **ወራት- ዓመት፡** ሶማሊላንድ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ቶጎ፡
- **ዓመታት፡** ኮንጎ፣ ኔፓል፣ ሶማሊያ

የብሄራዊ መግባባት ውጤት...



ምንጭ: Paffenholz, et al (2017). *What Makes or Breaks National Dialogues?* ገጽ 20

ክፍል 4፡ ማጠቃለያ

- በኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ እና የቅርብ ጊዜ የተጠራቀሙ ቁርሾዎች አሉ። ችግሮቹን ለመፍታት የተደረገ መሰረታዊ የብሄራዊ መግባባት የለም።
- ግጭቶች፣የዜጎች ሞት፣ መፈናቀል፣ ንብረት መጥፋት ወዘተ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል።
- ብሄር ተኮር ግጭቶች ተበራክተዋል።
- ኢትዮጵያ ስድስተኛውን ጠቅላላ ምርጫ ከማካሄዷ በፊት ብሄራዊ መግባባት ማካሄድ እና ማጠናቀቅ ያስልጋታል፣
- ከሁለት ዓማት ተኩል በፊት የተጀመረው ታሪካዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ከህዝቦች ፍላጎት ውጪ ሄዷል ብለው በርካቶች ማመን ጀምረዋል።

ማጠቃለያ፡ የቀጠለ.....

- የዝግጅት፣ የብሄራዊ መግባባት እና የትግበራ ምእራፎች በትክክል እና በአግባቡ ሊነደፉ ይገባል።
- የተሰካ ብሄራዊ መግባባት ጥልቅ የቴክኒክ እውቀት እና ልምድ ይፈልጋል፣ የባለሙያ ድጋፍ ወሳኝ ነው።
- መተማመን መፍጠር ለብሄራዊ መግባባት ስኬታማነት የመሰረት ድንጋይ ነው፣
- ብሄራዊ መግባባት ብሄራዊ አጀንዳ ነው- የውጭ ሀገራትና ድርጅቶች ተሳትፎ የተመጠነ ሊሆን ይገባል፣

ማጠቃለያ፡ የቀጠለ.....

- ብሄራዊ መግባባት መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣትም ሆነ የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ቀውሶችን ለመፍታት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፣
- ብሄራዊ መግባባት ለኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ብቸኛው መፍትሄ አይደለም።
  - ከብሄራዊ መግባባት የሚጠበቀው ውጤት የተጋነነ እንዳይሆን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፣
  - በጥንቃቄ ያልተዘጋጀ እና ያልተመራ የብሄራዊ መግባባት ሂደት ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ ሊያባብስ ይችላል፣

በመጨረሻ

- ብሄራዊ መግባባት ግልጸኝነት፣ ትእግስት፣ መደማመጥ እና የሌሎችን ሀሳብ ማክበርን ይጠይቃል ።

- **"I disapprove of what you say, but I will defend to the death your right to say it“**

  Voltaire

ተፈጸመ

አመሰግናለሁ